Att: To: ተያዥነት

# የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎችን አጠቃቀም መመሪያ /ለማሻሻል/ የወጣ መመሪያ ቁጥር 51/2000.

1. አውጪው ባለሥልጣን

የገቢዎች ሚኒስትር በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ስለመጠቀም ግዴታ በሚወስነው የሚንስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 139/1999 አንቀጽ22 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ያወጣውን መመሪያ ቁጥር 46/1999 ለማሻሻል ይህን መመሪያ አውጥቷል።

2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ« የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀምን በሚመለከት የወጣውን መመሪያ ቁጥር 46/1999 /ለማሻሻል /የወጣ መመሪያ ቁጥር 51//2000 » ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

3. ማሻሻያ

የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን አጠቃቀም በሚመለከት የወጣው መመሪያ ቁጥር 46/1999 ከዚህ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1. ከአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 14 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 15 ተጨምሯል።

"15) ማንኛውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በተለይም የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ እና/ወይም የፊስካል ፕሪንተር መሣሪያዎች አቅራቢ ለመሣሪያዎቹ ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡበት ጊዜ አንስቶ ለአምስት አመታት የሚቆይ መለዋወጫ ለማቅረብ ከመሣሪያዎቹ አምራች ጋር የገባዉን የዋስትና ውል ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት።"

2. ከአንቀፅ 9 ቀጥሎ የሚከተለው አንቀፅ 10 እንደ አዲስ ተካቷል።

"10. የሽያጭ መመዝገቢያ ነቋጣ ሶፍትዌር ፍላጎቶች

ገንቻ
ሚኒስትር

63

የሽያጭ መመዝገቢያ ነቋጣ ሶፍትዌር ሻጮች ለደንበኞቻቸው ሶፍትዌር ሲያቀርቡ ቀጥሎ የተመለከቱትን የአፈፃፀም ቅደም ተከተሎች መከተል ይጠበቅባቸዋል።

1. የሶፍትዌር ሻጭ የሽያጭ መመዝገቢያ ነቋጣ ሶፍትዌርን ከሽያጭ መመዝገቢያ ነቋጣ መሣሪያ ጋር ወይም ለብቻው ማቅረብ ይችላል።
2. ማንኛውም የሽያጭ መመዝገቢያ ነቋጣ ሶፍትዌር ሻጭ በባለሥልጣኑ ዘንድ ለለ ሶፍትዌሩ አቅራቢነት መመዝገብ እንዲሁም የሚያቀርበዉን ሶፍትዌር ማለመዝገብ ይኖርበታል፤ ለራሱ የአቅራቢነት፣ ለሚያቀርበዉም ሶፍትዌር የምዝገባ ምሥክር ወረቀት ሊኖረው ይገባል።
3. ማንኛውም የሽያጭ መመዝገቢያ ነቋጣ ሶፍትዌር ሻጭ በመመሪያው አንቀፅ ፲፩ ድንጋጌ መሠረት የአቅራቢነት ፅውቅና ለማግኘት የሚያስችለውን የአፈፃፀም ዋስትና ማቅረብ አለበት።
4. የሽያጭ መመዝገቢያ ነቋጣ ደረሰኝ ዴታ በደንቡ አንቀፅ 7.2 መሠረት በፈለካል ማተሚያው በተቀመጠው የኤሌክተሮኒክ ጆርናል ዉስጥ መቀመጥ አለበት።
5. ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ ነቋጣ ሶፍትዌር ከፈለካል ማተሚያ ሌላ ለደረሰኞች ህትመት መፍቀድ የለበትም።
6. ማናቸውም የሽያጭ ዴታ በኤሌክትሮኒክ ጆርናሉ ከመመዝገቡ በፊት በማንኛውም የኔትወርክ መሣሪያ ወይም ማጠረቀሚያ ላይ መፃፍ የለበትም።
7. የሽያጭ መመዝገቢያ ነቋጣ ሶፍትዌር ሻጮች የሶፍትዌራቸውን አወቃቀር የፅሑፍና ሰዕላዊ መግለጫ ዲዛይን ከሶፍትዌሩ ናሙና በመመሪያው አንቀፅ 12.1(ሠ) እና (ሠ) መሠረት ሶፍትዌሩን ለማስመዝገብ ማመልከቻ በሚያቀርቡበት ወቅት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለባቸው።
8. የሽያጭ መመዝገቢያ ነቋጣ ሶፍትዌር ሻጮች የሶፍትዌራቸውን አይነት በተገቢው ሁኔታ መጠበቅ የሚገባቸው ሲሆን በአዲስ መልክ የሚለቁትንም ሆነ የማሻሻያ ሶፍትዌር ባለሥልጣኑ ሳያውቀው በተጠቃሚዎች መሣሪያዎች ላይ መጫን የለባቸውም።



637

9. አዲስ ሶፍትዌር በተለቀቀ ጊዜ የሽያጭ መመዝገቢያ ነቋጣ ሶፍትዌር ሻጮች ስለ ሶፍትዌሩ ተግባራት፣ ከነባሩ ጋር ስለአለው ልዩነትና ለምን ልዩነቶቹ እንደተካተቱ የሚያስረዳ መረጃ ለባለሥልጣኑ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

10. የሽያጭ መመዝገቢያ ነቋጣ ሶፍትዌር

ሀ. የሽያጭ መመዝገቢያ ነቋጣ ማያ የሽያጭ ቁሳቁስን ስሞች ማየትና መምረጥ፣ የባዶ ወይም የመከነ እንዲሁም የተመላሽ አገልግሎቶች ይኖሩታል፤

ለ. እያንዳንዷን የተመዘገበች ሽያጭ በፊስካል ደረሰኝ ያትማል፤

ሐ. እያንዳንዷን የተመዘገበች ባድ በፊስካል ደረሰኝ ያትማል፤

መ. እያንዳንዷን የተመዘገበች ተመላሽ በፊስካል ደረሰኝ ያትማል፤

ሠ. ማናቸውንም ፊስካል ያልሆኑ ሰነዶች የፊስካል አርማ ወይም የፊስካል አርማ የሚመስል ምልክት በፊስካል ወይም ፊስካል ባልሆነ ማተሚያ እንዳይታተም መከልከል፤

ረ. የፊስካል ማተሚያው ወረቀት በሌለው ጊዜ ወይም ችግር በገጠመው ጊዜ የሽያጭ አገልግሎትን ማቆም።

11. የሽያጭ መመዝገቢያ ነቋጣ ሶፍትዌር ሻጭ በሶፍትዌሩ ባለ ስህተት ምክንያት ወይም በተገቢው ባልተስተካከለ የሶፍትዌሩ ደህንነት ችግር ምክንያት ለሚፈጠር ያልተገባ ሁኔታ ተጠያቂ ነው።

12. የሽያጭ መመዝገቢያ ነቋጣ ሶፍትዌር ሻጭ ሶፍትዌሩ የአለውን አገልግሎቶችን የቴክኖሎጂ ገፅታውን እንዲሁም የሚያስፈልገውን የመሳሪያ ፍላጎቶች ተጠቀሚዎች ምርጫ ይኖራቸው ዘንድ አዘጋጅቶ ማሠራጨት ይጠበቅበታል።

13. የሽያጭ መመዝገቢያ ነቋጣ ሶፍትዌር ሻጭ ለመሣሪያ አምራቾች የሠራው ሶፍትዌር ከሚያመርቷቸው የፊስካል ማተሚያዎች ጋር ይጣጣም እንደሆነ

መሳሪያ ፈቃጅ
ሚኒስቴር

የገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ቤተመጻሕፍት ዳይሬክቶሬት
Ministry of Revenues
Records and Documentation Section



638

በቂ መረጃ ማቅረብ የሚኖርበት ሲሆን ሶፍትዌሩን ከፊስካል ማተሚያዎች ጋር ለማጣጣም ተገቢውን ሶፍትዌር ማቅረብ አለበት።

14. የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌር የካርድ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ከሆነ የPayment Card Industry (PCI) Data Security Standards (DSS) guidelines (Payment Application Best Practices) ፍላጎቶች ማሟላት አለበት። ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌር ሻጭ ይህንን ለማሟላቱ ከካርድ አቅራቢው የምሥክር ወረቀት ማግኘት ይኖርበታል።

15. የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌር ሻጭ በባለሥልጣኑ የሚዘጋጀውን ደረጃዎችንና የደንቦችን ፍላጎቶች ለመጠበቁ የማረጋገጫ ፅሑፍ መፈረም አለበት።"

2. የቀድሞዎቹ ከአንቀጽ 10 እስከ 35 ያሉት ቁጥሮች ከአንቀጽ 11 እስከ 36 ተደርገዋል።

4. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስትር ተፈርሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ የፀና ይሆናል።

መላኩ ፈንታ
ሚኒስትር



639